# ስለ መንግስት እና ሳይንስ የኮርስ ማጠናቀቂያ (EOC) ፈተና
## በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

የሜሪላንድ አጠቃላይ የምዘና ፕሮግራም (MCAP)በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ይዘት ላይ የተማሪ እድገትን በተመለከተ ለመምህራን፣ ለወላጆች እና ለማህበረሰብ መረጃ ይሰጣል። ጠንካራ የምዘና ስርዓት በመዘርጋት፣ ባለድርሻ አካላት ትምህርት ቤቶች እንዴት እየሰሩ እንደሆኑ እና የተማሪን እድገትና ስኬት ለመደገፍ የቱ ጋ እርዳታ መደረግ እንዳለበት ያስገነዝባል።

ከ2023-2024 የትምህርት አመት ጀምሮ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ለሚገቡ ተማሪዎች (የመጀመሪያ ጊዜ ዘጠነኛ ክፍል (FTNG) 2024፣ 2027 የሚመረቁ)፣ ስለ መንግስት እና ስለ ሳይንስ ትምህርት የሜሪላንድ አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስነመንግስት እና የሳይንስ ኮርሶች የመጨረሻ ክፍል የተማሪዎች ምዘና 20 ፐርሰንት ይያዝላቸዋል። ይህ 20 በመቶ በሁለተኛው ሴሚስተር ወይም ሴሚስተር “B” የመጨረሻ ውጤት ይሰላል። የሴሚስተር “B” አጠቃላይ ውጤት ለእነዚህ ተደጋጋፊ ኮርሶች 3ኛ የማርክ መስጫ ጊዜ ውጤት (40%)፣ 4ኛ የማርክ መስጫ ጊዜ ውጤት (40%) እና MCAP የኮርስ ማጠቃለያ (EOC) የፈተና ውጤት (20%) ይሆናል። ተማሪዎች ለመመረቅ EOC ፈተናዎችን ማለፍ አይጠበቅባቸውም፣ ነገር ግን የኮርስ ክሬዲት ለማግኘት ኮርሱን ማለፍ አለባቸው። ከዚህ በታች MCAP ስነመንግስት እና የስነህይወት ሳይንስ የሜሪላንድ የተቀናጀ ሳይንስ ምዘና (LS MISA) EOC ፈተና በተማሪ የዘጠነኛ ክፍል ተመሳሳይ የመጨረሻ ክፍል 20% እንደሚቆጠር የሚያመለክት የሽግግር ጊዜ ማእቀፍ እነሆ።

| | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል | 11ኛ ክፍል | 12ኛ ክፍል |
|---|---|---|---|---|
| የትምህርት ዓመት (SY) 2023-2024 | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = ተሳትፎ ብቻ | EOC ፈተና = ተሳትፎ ብቻ | EOC ፈተና = ተሳትፎ ብቻ |
| የትምህርት ዓመት (SY) 2024-2025 | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = ተሳትፎ ብቻ | EOC ፈተና = ተሳትፎ ብቻ |
| የትምህርት ዓመት (SY) 2025-2026 | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = ተሳትፎ ብቻ |
| የትምህርት ዓመት (SY) 2026-2027 | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት | EOC ፈተና = 20% የኮርስ ውጤት |

የመመረቂያ መስፈርቶች የኮርስ ክሬዲቶችን፣ MCAP ምዘናዎች እና የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰዓቶችን ያካትታሉ። ስለ እያንዳንዱ የተማሪዎች የትምህርት ዘርፍ ልዩ የምረቃ መስፈርቶችን በሚከተለው ድረ ገጽ ላይ ሊያገኙ ይችላሉ፡
www2.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/graduation-requirements

MCAP ስለ መንግስት እና LS MISA EOC ፈተናዎችን የሚመለከቱ የኮርስ ኮዶች እና የኮርሶቹ ርዕሶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች MCAP ምዘና EOC ፈተና የሚሰጥባቸው ኮርሶች እነዚህ ናቸው። ተማሪዎች እነዚህን ኮርሶች በጊዜ መርሐግብር ካርዳቸው ላይ በኮርሱ መለያ መጨረሻ ላይ 'x' ተጽፎበት ያገኙታል።

| ስነመንግስት ኮርሶች | | LS MISA ኮርሶች | |
|---|---|---|---|
| የኮርስ መለያ | የኮርሱ ርእስ | የኮርስ መለያ | የኮርሱ ርእስ |
| SOC2003B | ብሔራዊ የስቴት እና የአካባቢ (NSL) ስነመንግሥት B/ National State and Local (NSL) Government B | SCI2000B | ባዮሎጂ B |
| SOC2004B | ኦነርስ ብሔራዊ የስቴት እና የአካባቢ (NSL) ስነመንግሥት B/Honors National State and Local (NSL) Government B | SCI2001B | ኦነርስ ባዮሎጂ B/Honors Biology B |
| SOC2025B | MCPS PIB ስነመንግስት B/MCPS PIB Government B | SCI2013B | የላቀ ሳይንስ 4 ባዮሎጂ B/Advanced Science 4 Biology B |
| SOC2083B | RMS ስነመንግስት B/RMS Government B | SCI2049B | የከባቢ ሳይንስ ባዮሎጂ B/Environmental Science Biology B |
| | | SCI2084B | MCPS PIB ባዮሎጂ B/MCPS PIB Biology B |
| | | SCI2103B | RMS ባዮሎጂ 1B/RMS Biology 1B |
| | | SCI2108 | ኦነርስ ባዮሎጂ ባለ ሁለት ክፍለጊዜ/Honors Biology Double Period |

### Q: አሁን ባለው MCAP EOC ፈተና እና ባለፈው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዘና (HSA) መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

A: HSA ምዘና መርሃ ግብር ተማሪ የመመረቂያ ምዘና ለማሟላት የማለፊያ ነጥብ የሚያገኝበት ተከታታይ የሁለተኛ ደረጃ ምዘና ነበር። ተማሪ በምዘናው ላይ ያሳየ(ች)ው አፈጻጸም በተማሪው(ዋ) የመጨረሻ ውጤት ላይ በኮርስ ወይም ተዛማጅ የኮርስ ክሬዲቶችን በማግኘት ላይ ምንም ተጽእኖ አልነበረውም።

MCAP EOC ፈተና በተማሪ የመጨረሻ ኮርስ ውጤት ላይ ይካተታል። ተማሪ EOC ፈተናን ማለፍ የተለየ የመመረቂያ መስፈርት ተደርጎ አይቆጠርም።

### Q: EOC በልዩ ሁኔታ የተሰናዱ ፈተናዎች አሉ?

A: አዎ፣ EOC ፈተናዎች በብሬይል፣ በአሜሪካ የምልክት ቋንቋ እና በትልልቅ ፊደላት ጉልህ ህትመት ይገኛሉ። እንደ ሁልጊዜው፣ በተማሪ የግለሰብ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፕሮግራም፣ 504 ፕላን እና/ወይም የእንግሊዘኛ ተማሪ እቅድ ውስጥ የሚገኙ የፈተና መሰናዶዎችን መከተል አለባቸው።

ከፍተኛ የግንዛቤ (ኮግኒቲቭ) እክል ያለባቸው ተማሪዎች ተለዋጭ ምዘናዎችን ለመውሰድ መመዝገብ ይችላሉ። አማራጭ ምዘናዎችን እንደአግባቡ ለመውሰድ ካልተመዘገቡ በስተቀር IEP እና 504s ያላቸው ተማሪዎች የተሰናዳውን EOC ፈተና መውሰድ አለባቸው። ተለዋጭ ምዘናዎችን የሚወስዱ ተማሪዎች በኮርሱ የመጨረሻ ውጤታቸው 20 በመቶ የሚሆነውን የምዘና ውጤት እንዲኖራቸው አይገደዱም።

### Q: EOC ፈተናዎች ከእንግሊዝኛ ውጪ በሌሎች ቋንቋዎች ይሰጣሉ?

A: 2023-2024 የትምህርት አመት እና ከዚያም በኋላ፣ EOC ፈተናዎች ለተማሪዎች በስፓኒሽኛ የተተረጎመ መሰናዶ ይኖራል።

## የኮርስ መጨረሻ (EOC) ውጤት አሰጣጥ

### Q: አንድ ተማሪ EOC ፈተና የሚጠበቅበ(ባ)ትን ኮርሶች ጨርሶ ካለፈ(ች) እና EOC ፈተና ካለፈ(ች) ቀጥሎ ምን ይደረጋል?

A: የማጠናቀቂያ ትምህርታቸው 20 በመቶ የሚሆነውን EOC ፈተና ወስደው ኮርሱን ያለፉ ተማሪዎች የመመረቂያ ምዘና መስፈርቱን አሟልተዋል።

### Q: አንድ ተማሪ EOC ፈተና ቢወድቅ ነገር ግን ኮርሱን ካለፈ ምን ይሆናል?

A: EOC ፈተና ለተማሪው(ዋ) የመጨረሻ ኮርስ ውጤት 20 በመቶውን ይይዛል። የመመረቂያ ምዘና መስፈርትን ለማሟላት EOC ፈተና ማለፍ ከአሁን በኋላ እንደ መስፈርት አይቆጠርም። ተማሪ የመጨረሻ ኮርስ ውጤት ካለፈ(ች) የኮርሱን እና የመመረቂያ መስፈርቶችን ምዘና ያሟላል።

### Q: ተማሪ ኮርሱን እና EOC ፈተና ቢወድቅ ምን ይሆናል?

A: ኮርሱን እና EOC ፈተና የወደቁ ተማሪዎች የማጠናቀቂያ ውጤት 20 በመቶ እንዲያዝላቸው EOC ፈተና ጋር ኮርሱን እንደገና መውሰድ አለባቸው። በአማራጭ፣ ተማሪዎች የኮርስ ክሬዲት ለማግኘት የትምህርት ቤቱን የተወሰነ የክሬዲት ኮርስ መውሰድ ይችላሉ። ሆኖም EOC ፈተና ውጤት እንደ መጨረሻ ውጤት 20 በመቶ አይቆጠርም።

### Q: በፈተና መስጫ ወቅት ተማሪ EOC ፈተናውን ካልወሰደ(ች) ምን ይደረጋል?

A: ተማሪው(ዋ) የቀረ(ች)በት ምክንያት ካለው/ካላት፣ ተማሪው(ዋ) የሴሚስተሩን ኮርስ እንዳላሟላ(ች) ይቆጠራል። አንዴ EOC ፈተና ከወሰዱ በኋላ የመጨረሻው የኮርስ ውጤት ከ EOC ፈተና የተገኘውን ውጤት በመጠቀም ይሰላል። ውጤቱን ለማሻሻል የተማሪው(ዋ) ካውንስለር MCPS ቅጽ 355-27C መሙላት ይኖርበታል። ተማሪው(ዋ) በህገ ወጥ መንገድ የቀረ(ች) (ማለትም ያለምክንያት መቅረት) ከሆነ፣ ተማሪው(ዋ) በመጨረሻው የኮርስ ውጤት ምዘና የሚሰላ ዜሮ (0) ያገኛል/ታገኛለች። በ COMAR የመመረቂያ መስፈርቶች መሰረት ተማሪው(ዋ) ዲፕሎማውን ለማግኘት አሁንም በምዘናው መሳተፍ ይኖርበ(ባ)ታል።

### Q: ተማሪዎች የኮርስ ውጤታቸውን ለማሻሻል EOC ፈተና እንደገና እንዲወስዱ ይፈቀድላቸዋል?

A: አይደለም፡ ተማሪዎች ከፍተኛ የኮርስ ውጤት ለማግኘት ከኮርሱ ተነጥሎ EOC ፈተና እንደገና መውሰድ አይችሉም።

### Q: የስነመንግስት እና LS MISA EOC ፈተና ውጤቶች የሚሰጡት መቼ ነው?

A: EOC ፈተና ውጤቶች የማርክ መስጫ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት StudentVue/ParentVue እና የመምህር የውጤት መጽሔት ላይ ይለጠፋሉ።

### Q: አንድ ተማሪ ባዮሎጂ A ወይም ብሄራዊ፣ ስቴት እና የአካባቢ አስተዳደር A ፈተና ከወደቀ(ች) EOC መውሰድ ይፈቀድለ(ላ)ታል?

A: አዎ፣ ምዘናው የሚሰላው በሴሚስተር B የመጨረሻ ውጤት ጋር ስለሆነ እስከዚያ EOC ፈተና ሊወስዱ ይችላሉ።

## አማራጮች እና ልዩ ሁኔታዎች

### Q: አንድ ተማሪ ከስቴት ውጭ ወይም ፐብሊክ ስኩል ካልሆነ ትምህርት ቤት የኮርስ ክሬዲት ያለው የብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና የአካባቢ አስተዳደር ወይም ባዮሎጂ ትምህርት ክሬዲት ይዞ ቢዛወር ምን ይደረጋል? ይህ ተማሪ EOC ፈተና መውሰድ ያስፈልገዋል?

A: የዝውውር ክሬዲት የመስጠት ያለፈው ልምድ ይቀጥላል። እነዚህን ክሬዲቶች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጭ ያገኘ(ች) ተማሪ የዝውውር ኮርስ እና የፈተና ክሬዲት ይሰጠዋል/ይሰጣታል፤ እና MCAP ስነመንግስት እና/ወይም LS MISA EOC ፈተና መውሰድ አያስፈልገውም/አያስፈልጋትም።

### Q: ለላቀ የስነመንግስት ትምህርት ምደባ (AP) ስነመንግስት ኮርስ EOC ይፈለጋል?

A: በላቀ ደረጃ ምደባ (AP) የአሜሪካ መንግስት ኮርስ የተመዘገቡ ተማሪዎች የምረቃ መስፈርቶቹን ለማሟላት ትምህርቱን እንዲያልፉ እና በመንግስት EOC ፈተና ወይም AP ፈተና መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። EOC ፈተና ውጤት የመጨረሻ የኮርስ ውጤታቸው እንደ 20% አይቆጠርም።

### Q: AP ባዮሎጂ ወይም ለኢንተርናሽናል ባካሎሬት (IB) ባዮሎጂ ኮርስ LS MISA EOC ፈተና ያስፈልጋል? ከሆነ፣ ባለፈው ዓመት ባዮሎጂ እና MCAP LS MISA የወሰዱ ተማሪዎችስ?

A: ተማሪ ከዚህ ቀደም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የባዮሎጂ ኮርስ እና MCAP LS MISA ከወሰደ፣ AP ባዮሎጂ ወይም IB ባዮሎጂ ኮርስ ከወሰደ(ች) EOC ፈተና እንደገና መውሰድ አያስፈልገውም። AP ባዮሎጂ የሚወስዱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመመረቂያ መስፈርቶቻቸውን ለማሟላት AP ፈተና ወይም LS MISA EOC ፈተና መውሰድ አለባቸው። EOC የባዮሎጂ ፈተና እንደ መጨረሻ የኮርስ ውጤት 20% አይቆጠርም። FNGSS የስነ ህይወት ሳይንስ ክሬዲት AP ወይም IB ባዮሎጂ የወሰዱ እና ባዮሎጂ ያልተማሩ ከአስረኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች AP ወይም IB ባዮሎጂ ፈተና በተጨማሪ LS MISA EOC ፈተና መውሰድ አለባቸው። ሆኖም የፈተና ውጤታቸው በተማሪ የመጨረሻ ሴሚስተር B ውጤት ላይ አይሰላም።

### Q: የኮሌጅ ባዮሎጂ ወይም የስነመንግስት ትምህርት (ጣምራ ምዝገባ) የሚወስዱ ተማሪዎች EOCs መውሰድ አለባቸው?

A: አዎ፣ ተማሪው(ዋ) ከዚህ ቀደም LS MISA ካልወሰደ(ች)፣ LS MISA EOC ፈተና መውሰድ ይኖርበ(ባ)ታል። ቀድሞ በተለዩት የፈተና ወቅቶች ፈተናዎችን ለመስጠት የት/ቤታቸው የፈተና አስተባባሪ ያገኛቸዋል። የፈተና ውጤታቸው በተማሪው የመጨረሻ ኮርስ ውጤት ጋር አይሰላም። በኮሌጅ ደረጃ ስለ መንግስት ኮርስ የክሬዲት መስፈርት የሚያሟላ የስነመንግስት ትምህርት የለም፣ ስለዚህ፣ MCAP ስነመንግስት ኮርስ EOC ከጣምራ ምዝገባ በፊት መወሰድ አለበት።

### Q: መጪዎቹ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EML) ዘጠነኛ ክፍል በሚገቡበት ዓመት የባዮሎጂ እና/ወይም የብሔራዊ፣ የስቴት እና የአካባቢ መንግሥት ኮርሶችን መውሰድ አለባቸው?

A: የኮርሱ ቅደም ተከተል የተሻሻለው በከፍተኛ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት ደረጃ ላይ ያሉ EMLs በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) *መመሪያ* መሰረት EOC ፈተናዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች EMLs ኮርስ ቅደም ተከተልን አስመልክቶ ነው። ስለዚህ፣ አብዛኛዎቹ EMLs እነዚህን ፈተናዎች በ10ኛ ክፍል ወይም በ11ኛ ክፍል፣ የእንግሊዘኛ የብቃት ደረጃቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲወስዱ ያስፈልጋል።

### Q: አዲስ የመጡ ተማሪዎች EMLs EOC ፈተናዎችን መውሰድ አለባቸው?

A: ከ12 ወራት በታች በት/ቤት የተመዘገቡ EML ተማሪዎች በተዛማጅ ኮርሶች ከተመዘገቡ EOC ፈተናዎችን መውሰድ አለባቸው። የመመረቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት ፈተና መውሰድ አለባቸው። ሆኖም፣ EFOC ፈተና ውጤት በኮርሳቸው የመጨረሻ ውጤት ላይ አይካተትም።